የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ መጋቢት ፳ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No. 21
ADDIS ABABA 29th March, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፺፱/፳፻፲፬

መተሐራ ስኳር ፋብሪካን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ................................ገጽ ፲፬ሺ፩፻፲፪

## Content

Regulation No. 499/2022

Metehara Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulation........................Page 14112

**ደንብ ቁጥር ፬፻፺፱/፳፻፲፬**

**<u>መተሐራ ስኳር ፋብሪካን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "መተሐራ ስኳር ፋብሪካን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፺፱/፳፻፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. መቋቋም**

፩/ መተሐራ ስኳር ፋብሪካ፣ ከዚህ በኋላ "ፋብሪካ" እየተባለ የሚጠራው፣ የፌደራል የመንግሥት ልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ መተሐራ ስኳር ፋብሪካ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

**REGULATION NO. 499/2022**

**<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF METEHARA SUGAR FACTORY</u>**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 47(1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as "Metehara Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulation No. 499/2022".

**2. Establishment**

1/ Metehara Sugar Factory, hereinafter referred to as "The Factory", is hereby established as a Federal Public Enterprise.

2/ Metehara Sugar Factory shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

፫. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀፅ ፭፻፶ መሠረት የፋብሪካውን የንግድ ስራ ጉዳዮች የመምራት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር የፋብሪካው ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል።

፬. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ ዋና መሥሪያ ቤት መተሐራ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌላ ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

፭. **ዓላማ**

ፋብሪካው የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ የሸንኮራ አገዳና ስኳር የሚያስገኙ ተክሎችን ማልማት፤

፪/ ስኳር፣ የስኳር ተረፈ ምርቶች እና ተጓዳኝ ምርቶችን ማምረት፤

፫/ ስኳር፣ የስኳር ተረፈ ምርቶችንና ተጓዳኝ ምርቶችን በኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ በኩል ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፤

፬/ የፋብሪካውን የስኳር ልማት ማስፋፊያ መልሶ የማደስ ፕሮጀክቶችን ማቀድና ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤

፭/ በአዋጪነትና በውጤታማነት ላይ ተመስርቶ እንደአስፈላጊነቱ ከአገዳ አብቃዮች ጋር ውል ገብቶ መስራት፤

፮/ ለፋብሪካው የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት መስራት፣

3. **Supervisory Authority**

Without prejudice to the right of the Ethiopian Sugar Industry Group Pursuant to Article 550 of the Ethiopian Commercial Code to direct the business affairs of the Factory, the Public Enterprises Holding and Administration shall be the Supervising Authority of the Factory.

4. **Head Office**

The Head Office of Metehara Sugar Factory shall be in Metehara town and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. **Purpose**

The purposes for which the Factory is established are:

1/ To grow sugarcane and other sugar yielding plants;

2/ To process and produce sugar, sugar by-products and co-products;

3/ To supply sugar and sugar by products and co-products to local as well as foreign market through the Ethiopian Sugar Industry Group;

4/ To plan sugar development expansion and overhaul projects within the Factory and implement same upon approval;

5/ To work in agreement with sugar cane growers based on feasibility and effectiveness;

6/ Work to produce the required trained manpower in number, type and quality;

፯/ ለሥራው አስፈላጊ የሆነውን የሸንኮራ አገዳ እርሻ መሬት በሊዝ ወይም በሌላ ሕጋዊ መንገድ ማግኘትና በይዞታው ስር ማድረግና ማልማት፤

፰/ የገንዘብ ሚኒስቴር የሚሰጠውን የፖሊሲ አቅጣጫና የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር የገንዘብ ምንጮች የብድር ውል ተደራድሮ በመፈረም ገንዘብ መደበር፣

፱/ የፋብሪካውን የማምረት አቅም የሚጨምሩ አዲስ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትን ሥልጠናንና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ከሌሎች ኩባንያዎች ጋር መደራደርና ውል መፈረም፣

፲/ በኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ ከሚከናወኑት በጋራ ማዕቀፍ ከሚገዙት ግዢዎች ውጪ ያሉትን የግዢ ውሎች በመዋዋል ግዢ መፈጸም፣

፲፩ ዓላማዎቹን ከግቡ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ሥራዎችን መሥራት፡፡

**፮. ካፒታል**

ለመተሐራ ስኳር ፋብሪካ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፪ ቢሊዮን, ፭፻፸፩ ሚሊዮን, ፻፺፭ ሺህ, ፱፻፹፬.፺፪ ሳንቲም (ሁለት ቢሊዮን አምስት መቶ ሰባ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አራት ብር ከዘጠና ሁለት ሳንቲም) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፮፻፵፪ ሚሊዮን, ፯፻፺፰ ሺህ, ፱፻፺፮.፳፫ ሳንቲም (ስድስት መቶ አርባ ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከሃያ ሶስት ሳንቲም ) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

7/ Acquire use right on lease or by other legal means and develop agricultural land for sugar cane plantation;

8/ In accordance with the policy direction and Directives issued by the Ministry of Finance, Negotiate and sign loans with domestic as well as foreign financial institutions;

9/ Enter into a contract with other companies for introducing new technologies or training and other matters of importance that improve the factory's productivity;

10/ Execute procurements those are not included in the common procurement package that is carried out by The Ethiopian Sugar Industry Group;

11/ Engage in any other activity that is necessary to accomplish its purposes.

**6. Capital**

The Authorized Capital of Metehara Sugar Factory is Birr 2,571,195,984.92 (Two billion Five hundred seventy one million one hundred ninety five thousand nine hundred eighty four birr and ninety two cents) of which Birr 642,798,996.23 (Six hundred forty two million seven hundred ninety eight thousand nine hundred ninety six birr and twenty three cents) is paid up in cash and in kind.

፯. **ኃላፊነት**

ፋብሪካው ካለው ጠቅላላ ሀብት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፰. **የቆይታ ጊዜ**

መተሐራ ስኳር ፋብሪካ ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል፡፡

፱. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ዓብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

7. **Liability**

The Factory shall not be held liable beyond its total assets.

8. **Duration**

The Factory is established for an indefinite duration.

9. **Effective Date**

This Regulation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 29th Day of March, 2022**

**ABIY AHMED (DR)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**